# ቤት እንዳይወሰድ ማገድ (Foreclosure Prevention) በኮቪድ-19 (COVID-19) አደገኛ ወቅት

**(ፌብሩአሪ 7 ቀን 2021 የተሻሻለ)**


ቤት የገዛሁበትን ብድር ለመክፈል እየተቸገርኩ ነው፡ ምን አማራጮች አሉኝ?

ትእግስት እንዲያደርጉ ወይም ግዜ እንዲሰጠኝ እንዴት ነው የምጠይቀው?

በመንግስት የተደገፈ ክፍያ ወይም ሞርጌጅ ሲባል ምንድነው፤ ይህ እንዳለኝ በምን አውቃለሁ?

ስለዚህ የቤት ዕዳዬ በመንግስት የተደገፈ ነው፤ ምን ማለት ነው?

የተሰጠኝ ግዜ ካለፈ በኋላ ምን ይሆናል ?

ቤቴ እንዳይወሰድ እየሰጋሁ ነው ይህ በኮቪድ ወቅት ሊሆን ይችላልን?

በዲሲ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በይቆይ የተያዘ የቤት ጉዳይ አለኝ; ፍርድ ቤት መቅረብ አለብኝን?

ያለኝን የብድር ዕዳ ባለመክፈሌ ቤቴ በፎርክሎዠር ተይዟል የሚል የፍርድ ቤት ጥሪ ደረሶኛል። ለዚህ መልስ መስጠት አለብኝ ?

በዚህ በቤቴ የመወሰድ ጉዳይ የሆነ ነገር ማቅረብ አለብኝን እንዴትሳ ነው የማደርገው?

ከዚህ ከኮቪድ በፊት ቤቴን አጥቼአለሁ፤ አሁን ከቤቴ ልባረር እችላለሁን?

የኮንዶሚኒየም ክፍያን ከመክፈል ወደ ኋላ ቀርቻለሁ ምን ማድረግ አለብኝ?

የንብረት ግብርም በመክፈል ረገድ ሳልከፍል ቆይቻለሁ ምን ማድረግ አለብኝ ?

በምከፍለው የቤት ሞርጌጅ ወይም ሌሎች የቤት ወጪዎች ሊረዱኝ የሚችሉ እርዳታዎች አሉን?

**ቤት የገዛሁበትን ገንዘብ ለመክፈል በችግር ላይ እገኛለሁ። ምን አማራጮች አሉኝ?**

የቤት ግዢ ብድሮን ለመክፈል አሁንም የሚችሉ ከሆነ መክፈሎን ይቀጥሉ። ይህንን ብድር ለመክፈል ፍጹም የማይችሉ ከሆነ ግን አማራጮች አሎት ግን የሚመጡት ከአስጊ ሁኔታዎች ጋር ነው።

የገንዘብ ወይም የገቢ ችግር ያጋጠሞት በዚህ በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት ከሆነ፤ በሚከፍሉት ላይ ግዜያዊ ቅነሳ (ፎርቤራንስ) ለማግኘት ሊያገኙ ይችል ይሆናል። ፎርቤራንስ ማለት አሁን ይሚከፍሉይ የወራዊ ክፍያ ለትንሽ ጊዜ ሊቀንስ ወይም ልቆም ይችላል። ያልተከፈለውን ክፍያ ወደኃላ መክፈል ይኖርብዎታል። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ እነዚያ ክፍያዎች ቀስ በቀስ በሂደት ወይም ቤትዎ ሪፋይናንስ ወይም ከሸጡ በኃላ መክፈል ይችላሉ።

ወይም ክፍያው ባጠቃላይ በይቆይ እንዲያዝሎት ማድረግ ይችላሉ። ግን ቆየት ብለው መክፈል አለቦት።

የዲሲ መንግስት የቤት ባለቤቶችን (የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም) ለመርዳት አዲስ የፌደራል መንግስት ገንዘብ ያገኛል። **የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም፤** የቤት ዕዳቸውን ለመክፈል ወደኋላ የቀሩ፤ ኮንዶ ገዝተው መክፈል ያቃታቸው፤ ለቤት ባለቤቶች ማህበር መክፈል ያለባቸው፣ የጋራ ትብብር ዕዳ ያለባቸው፣ የንብረት ግብር የሚከፍሉና የመብራት፣ ውሃ፤ ጋዝ ክፍያቸውን ለመክፈል ላልቻሉ ሰዎች ገንዘብ የሚሰጥ ነው። ይህ የሚሰጥ ገንዘብ እንደ ስጦታ የሚሰጥና መመለስ የማያስፈልገው ነው። ይህ የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም (Homeowner Assistance Fund) ገና አልተከፈተም/ አልተጀመረም ግን እርዳታውን ለማግኘት ብቁ ናቸው ለተባሉ ሁሉ በሚመጣው ጸደይ 2022 ( Spring 2022) ይጀመራል ተብሎ ይጠበቃል። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር (202) 540-7407 ይደውሉ ወይም ወደ af.dhcd@dc.gov ኢሜል ያድርጉ።

ለዲሲ ፎርክሎዠር መከላከያ ስልክ መስመር በ 202-265-2255 በመደወል ስላልዎት አማራጮች ከቤት ጉዳይ አማካሪ ጋር መነጋገር ይችላሉ።

**ትእግስት እንዲያደርጉ ወይም ግዜ እንዲሰጠኝ እንዴት ነው የምጠይቀው?**

የቤት ብድሮን ባገኙበት ወቅት ያገዞትን የሞርትጌጅ (mortgage) ሰው ጋር ተገናኙ (በየወሩ የክፍያዎን ሪፖርት የሚልክሎ ድርጅት ማለት ነው)። ወድያውኑም በየወሩ በሚከፍሉት ክፍያ ላይ ቅነሳ እንዲደርግሎት ወይም ክፍያው በአጠቃላይ እንዲታግድሎ ይጠይቁ። ጥያቄዎን ሲያቀርቡ፡ ይህንን በመጠየቅ ላይ ያሉት፤ በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት ገንዘባዊ ችግር እያገጠሞት ላይ በመሆኑ መሆኑን ያስረዱ።

ተበዳሪዎች ያላቸው የቤት ብድር “የመንግስት ድጋፍ” ያለው ከሆነ፤ የተወሰኑ ተጨማሪ መንቶችና መከላከያዎች አሎት”።የቤት ብድሮ “የመንግስት ድጋፍ”  ይኑረው አይኑረው፤ ምን ዓይነት ቅነሳ እንደሚደርጎት ይወስናል።

**በመንግስት የተደገፈ ክፍያ ወይም ሞርጌጅ ሲባል ምንድነው፤ ይህ እንዳለኝ በምን አውቃለሁ?**

“በመንግስት የተደገፈ” ሞርጌጅ ማለት ባለቤቶቹ ፤ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር (Federal Housing Administration (FHA)፣ የአሜሪካ የእርሻ ክፍል (the U.S. Department of Agriculture (USDA)፣ የአሜሪካ የስንኩላን ጉዳይ ክፍል (U.S. Department of Veterans Affairs (VA)፣ በፋኒ ሜ (Fannie Mae) ወይም ፍሬዲ ማክ (Freddie Mac) መንግስታዊ ድርጅቶች ሲሆኑ ወይም ኢንሹራንሱ በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱ ክፍሎች የተሸፈነ ሞርጌጅ ማለት ነው። ስለዚህ በ “በመንግስት የተደገፈ”  ሞርጌጅ እንዳሎትና እንደሌሎት ለማወቅ ወደ ሚከተለው here ገብተው ያጣሩ። የእኔ ሞርጌጅ በመንግስት የተደገፈ ነው። ታድያስ?

**ስለዚህ የቤት ዕዳዬ በመንግስት የተደገፈ ነው፤ ምን ማለት ነው?**

በመንግስት ህግ መሰረት የተወሰኑ መብቶችና ጥበቃዎች/መከለከያዎች አሎት። ለምሳሌ ቅነሳ ((forbearance) እንዲደርግሎት ከጠየቁ በኋላ፤ አበዳሪዎ ሌሎች ተጨማሪ አጋዥ ዶኩመንቶችን እንዲያቀቡ ሊጠይቆት አይገባም። የኮቪድ (COVID-19) ችግር ከመጀመሩ በፊትም ቢሆን የመክፈል ችግር ያጋጠሞት፤ አሁንም  ቅነሳውን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

በማእከለዊው መንግስት ህግ መሰረት፤ ከኮቪድ ጋር በተዛመደ መልኩ፡ ቅነሳ እንዲደረግሎ ብቁ ሁነው ከተገኙ፤ አበዳሪዎ እስከ **180 ቀናት** የሚቆይ የቅነሳ ግዜ ወይም ያለመክፈል ሁኔታ ሊሰጦት ይገባል፤ ከጠየቁ ደግሞ **ተጨማሪ የ180 ቀናት ግዜ** ሊሰጦት ይገባል።

**የተሰጠኝ ግዜ ካለፈ በኋላ ምን ይሆናል ?**

ይህ እንግዲህ የሚሞረከሰው በወሰዱት ብድር ዓይነት ነው። በአጠቃላይ አበዳሪዎችዎ የሚከተሉትን እንድታደርጉ ሊጠይቁዎት ይችላሉ፡

- ሳይከፍሉት የቀረውንና በቅናሽ እንዲከፍሉ የተደረጉትን ገንዘብ በሙሉ ግዜው ሲያበቃ ለምሳሌ የሶስት ዓመት ግዜ ካለፈ በኋላ በሙሉ ክፈሉ ሊሉ ይችላሉ።
- ቅነሳ የተደረገባቸው ክፍያዎች ተከፍለው እስኪጠናቀቁ በየወሩ ከለድሮው ከፍ ያለ ክፍያ እንዲከፍሉ ሊያደርጉ ይችላሉ።ቅነሳ የተደረገበትን ክፍያ ወይም ግድፈት የተደረገበትን ክፍያ

በሙሉ የብድሮ መጨረሻ ላይ በሙሉ እንዲከፍሉ ወይም በብድር ማለቅያው ግዜ ከፍለው እስኪጨርሱ ድረስ ቀኑን ማራዘም፤ወይም ንብረቱ ሲሸጡ ወይም እንደገና ሪፋይናንስ ሲያስደርጉ ሊያስከፍሎት ይችላል።

- የብድር ማስተካከያ እንዲደረግሎት መጠየቅ። ይህም ማለት ቅነሳ የተደርገባቸው ክፍያዎች ሁሉ ወደ መጨረጻው ክፍያ ተደምረው በየወሩ የሚከፍሉት በአዲስ የአከፋፈል ሁኔታ ተቀይሮ አዲስ ክፍያ ማመቻቸት

ይህንን የብድር ቅነሳ  እርምጃ ከመውሰዶ በፊት፤ መጨረሻ ላይ ምን አይነት የአከፋፈል ሁኔታ አበዳሪዎችዎ  እንደሚያደርጉ መጀመርያ ይጠይቁ። ስለአከፋፈሉ የሚያሳስብ ነገር ካጋጠሞት ጠበቃ ወይም የቤት አማካሪዎችን አነጋግሩ።

የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም፤ የቤት ዕዳቸውን ለመክፈል ወደኋላ የቀሩ፤ ኮንዶ ገዝተው መክፈል ያቃታቸው፤ ለቤት ባለቤቶች ማህበር  መክፈል ያለባቸው፣ የጋራ ትብብር ዕዳ ያለባቸው፣ የንብረት ግብር የሚከፍሉና የመብራት፣ ውሃ፤ ጋዝ ክፍያቸውን ለመክፈል ላልቻሉ ሰዎች ገንዘብ የሚሰጥ ነው። ይህ የሚሰጥ ገንዘብ እንደ ስጦታ የሚሰጥና መመለስ የማያስፈልገው ነው። ይህ የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም (Homeowner Assistance Fund) ገና አልተከፈተም/ አልተጀመረም ግን እርዳታውን ለማግኘት ብቁ ናቸው ለተባሉ ሁሉ በሚመጣው ጸደይ 2022 ( Spring 2022) ይጀመራል ተብሎ ይጠበቃል። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር (202) 540-7407  ይደውሉ ወይም ወደ af.dhcd@dc.gov ኢሜል ያድርጉ።

**ቤቴ እንዳይወሰድ እየሰጋሁ ነው ይህ በኮቪድ ወቅት ሊሆን ይችላልን?**

ግዚያዊ የዲሲ ሕግ፤  ባለቤቱ  ወይም ወራሾቹ ገና በውስጡ በመኖር ላይ ያሉና በባንክ የተያዘን ቤት በተመለከተ፤ የቤት ብድሮን አልከሉም፤ የንብረት ግብር አልከፈሉም፤  የኮንዶ ዕዳ አለቦት እየተባለ ሰውን ማስወጣት የተከለከለ መሆኑን ይገልጻል። ይህ ባለቤቱ  ወይም ወራሾቹ ገና በውስጡ በመኖር ላይ ያሉና በባንክ የተያዘ ቤት ሕግ እስከ **ሰኔ (ጁን) 30 ቀን 2022** እንዲቆይ ተራዝሚል።

በተጨማሪም፤ ባለቤቱ  ወይም ወራሾቹ የሚኖሩበት ቤት ላይ የሞርጌጅ ቤት መዝጋት የክስ ጉዳይ ያለዎት ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በዝህ በተጠበቀው ጊዜ ውስጥ በአጠቃላይ ውሳኔ አይሰጥም፡፡

እንዲሁም አብዛኛዎቹ አበዳሪዎች፤ ቤቱን የመዝጋት እርምጃ (foreclosure)ን በተመለከተ  የብድር እዳ የመክፈል ተግባር ከቆመ እስከ 120 ቀናት ድረስም  ምንም ማድረግ አይችሉም።

**በዲሲ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በይቆይ የተያዘ የቤት ጉዳይ አለኝ; ፍርድ ቤት መቅረብ አለብኝን?**

አንዳንድ የፍርድ ቤት የመኖሪያ ቤት መዘጋት ክሶች፤ በርቀት (በስልክ ወይም በቪዲዮ) እንዲቀጥሉ ቀነ ቀጠሮ እየተያዘላቸው ነው። በእርስዎ የክስ መዝገብ ላይ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በርቀት ለማየት የወሰነ ከሆነ፣ ችሎቱ ላይ እንዴት እንደሚገኙ ፍርድ ቤቱ መመሪያዎችን ይልክሎታል። ነባር የሆነ የመኖሪያ ቤት መዘጋት ክስ መዝገብ ያለዎት እና በቅርብ የሚደረግ የርቀት ሰሚ ችሎት ወይም ሌሎች የፍርድ ቤት ጉዳዮች እንዳለዎት እርግጠኛ ካልሆኑ፣ የክስ መዝገብዎ ያለበትን ደረጃ አንላይን ወይም የማህበራዊ ክፍል ጽሕፈት ቤት ሠራተኛ ቢሮ (Civil Division Clerk's Office) (202-879-1133) በመደወል መጠየቅ ይችላሉ።

## ያለኝን የብድር ዕዳ ባለመክፈሌ ቤቴ በፎርክሎዠር ተይዟል የሚል የፍርድ ቤት ጥሪ ደረሶኛል። ለዚህ መልስ መስጠት አለብኝ ?

አዎን። ግን እንደደንቡ  ያገኙት ከነበረው የ 21 ቀናት ግዜ ተጨማሪ ግዜ አሎት። የሚወክላቸው ጠበቃ የሌላቸው ሰዎች፤ የመልስ መስጠት ግዜ እስከ ጥር 15 ቀን 2021 እንዲቆይ ተደርጓላቸዋል። ይህም ማለት ቤትዎን እንዲለቁ የተነገሮት ከመጋቢት 18 ቀን 2020 በሁላ ከሆነ፤  መልስ ለመሰጠት ከጥር 15 2021 በሁላ የ 21 ቀናት ግዜ አሎት ማለት ነው (የ21 ቀናት ተጨማሪ ግዜው መቆጠር የሚጀምረው ከተነገሮት ቀን በሁላ ነው)።

## በዚህ ቤት የመወሰድ(ፎርክሎዠር) ጉዳዬ ላይ አንድ ነገር ማስገባት ካለብኝ እንዴት ነው ማድረግ ያለብኝ ?

የጸሃፊው  መስርያ ቤት የሲቪል ክፍሉ(The Civil Division Clerk's Office) ከሩቅ (remote) ሆኖ የሚሰራ ሲሆን፤ ዶኩመንቶችን  እንዴት ማስገባት እንደሚቻልና የሚከፈሉ ክፍያዎች እንዲነሱ አንዴት እንደሚጠየቅ መመርያዎቸን (instructions) አሰራጭቷል።

## ከዚህ ከኮቪድ በፊት ቤቴን አጥቼአለሁ፤ አሁን ከቤቴ ልባረር እችላለሁን?

ከቤትዎ እንዲባረሩ ለማድረግ፤ አዲሱ የንብረትዎ ባለቤት፤ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባል እና ከቤትዎ ለማስወጣት ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይኖርበታል። የቤቱ  ለሽያጭ ቢቀርብም፤ ወደያውኑ ከቤት መውጣት አለቦት ማለት አይደለም። ቤቱን ለሽያጭ ባቀረበ የቤት ባለቤት እንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ ከደረስብዎ፤ ከጠበቃ ጋር መነጋገር ሊያስፈልጎ ነው ማለት ነው።

## የኮንዶሚኒየም ክፍያን ከመክፈል ወደ ኋላ ቀርቻለሁ ምን ማድረግ አለብኝ?

ለኮንዶዎ ብድር ክፍያ በየወሩ መክፈል ካለቦት ገንዝበ ትንሽ ከፍ አድርገው መክፈል የሚችሉ ከሆነ የኮንዶዎቹ ማህበርን አግተኘው አንድ ዓይነት የአከፋፈል እቅድ ለማውጣት ተነጋገሩ።

ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻላችሁ፤ ሞርጌጅ ለማግኘት የረዳዎት ሰው ጋር ተነጋገሩና እዳዎን ለመክፈል እንደተቸገሩ ግለጹለት። ከተቻለ በየወሩ መክፈል የሚገባዎትን ግን ሳይከፍሉ ያለፎበትን ክፍያ፤ እርሱ ራሱ

ይከፍልና ፤ እርስዎ መክፈል የሚገባዎትን በብድሮ መጨረሻ ላይ እንዲከፍሉ ሊያደርግ ይችላል። ስለዚህ የቤት እዳዎ ከኮንዶ ማህበሮ ጋር ከሚሆን ከሞርጌጅ ተቋምዎ ጋር ይሆናል። የበለጠው ነገር ደግሞ የሞርጌጅ ተቋሞ ጋር ከመነጋገሮ በፊት ግን መጀመርያ ከጠበቃ ጋር ቢናግሩ ነው።

የኮንዶዎን ክፍያ ከመክፈል ወደ ኋላ የቀሩ ከሆነ፤ ሁሌም ቢሆን የሚመጣሎትን ደብዳቤዎች በደንብ ማየት አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም የኮንዶ ማህበሮ ዕዳዎን አልከፈሉም ብሎ የፎርክሎዠር ማስታወቅያ ሊልክሎት ይችላልና። እንዲህ ዓይነቱ ማስታወቅያ ከተላከሎት ከ 32 ቀናት በኋላ ቤትዎ ለሽያጭ ጨረታ ይቀርባልና። ይሁንና፤ በኮቪድ ወረርሽኙ ምክኛት፤ የዲሲ ግዜያዊ ህግ፤ ባለቤቶቹ ወይም ወራሾቹ ለሚኖሩበት ኮንዶ፤ ክፍያ ስላልከፈሉ፤ ኮንዶን ለሽያጭ ጨረታ ማቅረብ የተከለከለ ነው። ይህ ባለቤቱ ወይም ወራሾቹ የሚኖሩበት ቤት በባንክ ፎርክሎዠር እንዳይደረግ የወጣው ህግ እስከ **ጁን(ሰኔ) 30 ቀን 2022** ድረስ ተራዝሟል። የኮንዶዎ ማህበር **ከጁን 30 ቀን** 2022 በፊት ቤትዎን ለገበያ ለማዋል ከሞከረ ግን ወደያውኑ ጠበቃ ማነጋገር አለቦት።

በሚመጣው ጸደይ 2022 ( Spring 2022) ይጀመራል ተብሎ በሚጠበቀው የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም (Homeowner Assistance Fund) ማመልከቻው ሲከፈት ማመልከት ሊፈልጉ ይችላሉ። የዲሲ አስተዳደር ወይም መንግስት ከማእከላዊው መንግስት የቤት ባለቤቶችን ለመርዳት ገንዘብ እያገኘ ነው። **የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም፤** የቤት ዕዳቸውን ለመክፈል ወደኋላ የቀሩ፤ ኮንዶ ገዝተው መክፈል ያቃታቸው፤ ለቤት ባለቤቶች ማህበር መክፈል ያለባቸው፣ የጋራ ትብብር ዕዳ ያለባቸው፣ የንብረት ግብር የሚከፍሉና የመብራት፣ ውሃ፤ ጋዝ ክፍያቸውን ለመክፈል ላልቻሉ ሰዎች ገንዘብ የሚሰጥ ነው። ይህ የሚሰጥ ገንዘብ እንደ ስጦታ የሚሰጥና መመለስ የማያስፈልገው ነው። ይህ የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም (Homeowner Assistance Fund) ገና አልተከፈተም/ አልተጀመረም ግን እርዳታውን ለማግኘት ብቁ ናቸው ለተባሉ ሁሉ በሚመጣው ጸደይ 2022 ( Spring 2022) ይጀመራል ተብሎ ይጠበቃል። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር (202) 540-7407 ይደውሉ ወይም ወደ af.dhcd@dc.gov ኢሜል ያድርጉ።

ነገር ግን በ20019፣ 20020፣ 20024 እና 20032 ዚፕ ኮድ ውስጥ አንዳንድ የብቁነት ጥያቄዎችን የሚያሟሉ የኮንዶ ባለቤቶችን የሚረዳ የሙከራ ፕሮግራም( *pilot program)* ተጀምሯል። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ብቁ ሆኖ ለመገኘት ይህንን ቤት የገዙት፤ ለምሳሌ እንደ ኤች-ፒ-ኤ-ፒ ብድር( HPAP) ለመዝግያ ዋጋና ለቀብድ ክፍያ፤ ከ ቤቶችና የማህበረሰብ እድገት ክፍል (Department of Housing and Community Development) እርዳታ ያገኙ መሆን አለቦት። ስለየቤት ባለቤቶች የእርዳታ ፕሮግራም በበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ እዚህ ላይ here ይጫኑ።

**የንብረት ግብርም በመክፈል ረገድ ሳልከፍል ቆይቻለሁ ምን ማድረግ አለብኝ ?**

በራስዎ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ፤የሚከፍሉት የንብረት ግብር በተቻለ መጠን በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ የዲሲ የግብር ክፍልን አነጋገሩ (D.C. Office of Tax and Revenue) (ኦ-ቲ-አር OTR)። በ ሆምስቴድ (Homestead) ወይም ዕድሜያቸው የገፉ ዜጎች፤ ንብረት ያላቸው ስንኩላን የግብር ቅነሳ (Senior Citizen or Disabled Property Owner Tax Deduction) አማካኝነት  በሚከፍሉት የንብረት ክፍያ ላይ ቅናሽ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

የንብረት ግብሮን በቀጥታ የመክፈል ሃላፊነት ካለቦ( ምናልባትም ለቤት የሚከፈል ዕዳ የሌሎት ሊሆን ይችላል ወይም የሞርጌጅ አቀላጣፊው ራሱ የማይከፍለው ከሆነ)፤ እርስዎ ደግሞ መክፈል ካቃቶት፤ ኦ-ቲ-አርን( OTR) በማነጋገር ቀለል ያለ የአከፋፈል ዕቅድ ለማውጣት ይችሉ ይሆናል። በአጠቃላይ፣ የንብረት ግብር ክፍያዎን በመክፈል ረገድ፤ በየወሩ በደንብ የማይከፍሉ ከሆነ፤ መጨረሻ ላይ ቤትዎ ጨረታ ውስጥ ይገባ ይሆናል። ሆኖም ግን፣ በወረርሽኙ የተነሳ ዲስትሪክቱ እስከ  2021 ድረስ እንደዚህ አይነት በግብር የተነሳ የሚደረጉ፤ ነዋሪዎቹ እዛው በመኖር ላይ እያሉ፤ የቤት እገዳ ሽያጮችን እንደማያከናውን አሳውቋል።

ግዚያዊ የዲሲ ሕግ፤  ባለቤቱ  ወይም ወራሾቹ ገና በውስጡ በመኖር ላይ ያሉና በባንክ የተያዘን ቤት በተመለከተ፤ የቤት ብድሮን አልከሉም፤ የንብረት ግብር አልከፈሉም፤  የኮንዶ ዕዳ አለቦት እየተባለ ሰውን ማስወጣት የተከለከለ መሆኑን ይገልጻል። ይህ ባለቤቱ  ወይም ወራሾቹበውስጡ በመኖር ላይ ያሉና በባንክ የተያዘ ቤት ሕግ እስከ **ሰኔ 30 ቀን 2022** እንዲቆይ ተራዝሟል።

በሚመጣው ጸደይ 2022 ( Spring 2022) ይጀመራል ተብሎ በሚጠበቀው የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም (Homeowner Assistance Fund) ማመልከቻው ሲከፈት ማመልከት ይችላሉ። የዲሲ አስተዳደር ወይም መንግስት ከማእከላዊው መንግስት የቤት ባለቤቶችን ለመርዳት ገንዘብ እያገኘ ነው። ይህ ፕሮግራም የቤት ባለቤቶች የእገዛ ገንዘብ ( Homeowner Assistance Fund) በመባል ይታወቃል። **የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም፤** የቤት ዕዳቸውን ለመክፈል ወደኋላ የቀሩ፤ ኮንዶ ገዝተው መክፈል ያቃታቸው፤ ለቤት ባለቤቶች ማህበር  መክፈል ያለባቸው፣ የጋራ ትብብር ዕዳ ያለባቸው፣ የንብረት ግብር የሚከፍሉና የመብራት፣ ውሃ፤ ጋዝ ክፍያቸውን ለመክፈል ላልቻሉ ሰዎች ገንዘብ የሚሰጥ ነው። ይህ የሚሰጥ ገንዘብ እንደ ስጦታ የሚሰጥና መመለስ የማያስፈልገው ነው። ይህ የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም (Homeowner Assistance Fund) ገና አልተከፈተም/ አልተጀመረም ግን  እርዳታውን ለማግኘት ብቁ ናቸው ለተባሉ ሁሉ በሚመጣው ጸደይ 2022 ( Spring 2022) ይጀመራል ተብሎ ይጠበቃል። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር (202) 540-7407  ይደውሉ ወይም ወደ af.dhcd@dc.gov ኢሜል ያድርጉ።

ነገር ግን በ20019፣ 20020፣ 20024 እና 20032 ዚፕ ኮድ ውስጥ አንዳንድ የብቁነት ጥያቄዎችን የሚያሟሉ የኮንዶ ባለቤቶችን የሚረዳ የናሙና ፕሮግራም( *pilot program)* ተጀምሯል። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ብቁ ሆኖ ለመገኘት ይህንን ቤት የገዙት፤ ለምሳሌ እንደ ኤች-ፒ-ኤ-ፒ ብድር( HPAP) ለመዝግያ ዋጋና ለቀብድ ክፍያ፤ ከ ቤቶችና የማህበረሰብ እድገት ክፍል (Department of Housing

and Community Development) እርዳታ ያገኙ መሆን አለቦት። ስለየቤት ባለቤቶች የእርዳታ ፕሮግራም በበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ እዚህ ላይ here ይጫኑ።

**በምከፍለው የቤት ሞርጌጅ ወይም ሌሎች የቤት ወጪዎች ሊረዱኝ የሚችሉ እርዳታዎች አሉን?**

**የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም፤** የቤት ዕዳቸውን ለመክፈል ወደኋላ የቀሩ፤ ኮንዶ ገዝተው መክፈል ያቃታቸው፤ ለቤት ባለቤቶች ማህበር መክፈል ያለባቸው፣ የጋራ ትብብር ዕዳ ያለባቸው፣ የንብረት ግብር የሚከፍሉና የመብራት፣ ውሃ፤ ጋዝ ክፍያቸውን ለመክፈል ላልቻሉ ሰዎች ገንዘብ የሚሰጥ ነው። ይህ የሚሰጥ ገንዘብ እንደ ስጦታ የሚሰጥና መመለስ የማያስፈልገው ነው። ይህ የቤት ባለቤቶች የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም (Homeowner Assistance Fund) ገና አልተከፈተም/ አልተጀመረም ግን እርዳታውን ለማግኘት ብቁ ናቸው ለተባሉ ሁሉ በሚመጣው ጸደይ 2022 ( Spring 2022) ይጀመራል ተብሎ ይጠበቃል። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር (202) 540-7407 ይደውሉ ወይም ወደ af.dhcd@dc.gov ኢሜል ያድርጉ።

የዲሲው የቤት ባለቤቶች እገዛ ገንዘብ ገና አልተጀመረም እና በጸደይ 2022 ( Spring 2022) ይጀመራል ተብሎ ይጠበቃል። በ20019፣ 20020፣ 20024 እና 20032 ዚፕ ኮድ ውስጥ አንዳንድ የብቁነት ጥያቄዎችን የሚያሟሉ የኮንዶ ባለቤቶችን የሚረዳ የናሙና ፕሮግራም( *pilot program)* ተጀምሯል። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ብቁ ሆኖ ለመገኘት ይህንን ቤት የገዙት፤ ለምሳሌ እንደ ኤች-ፒ-ኤ-ፒ ብድር( HPAP) ለመዝግያ ዋጋና ለቀብድ ክፍያ፤ ከ ቤቶችና የማህበረሰብ እድገት ክፍል (Department of Housing and Community Development) እርዳታ ያገኙ መሆን አለቦት። ስለየቤት ባለቤቶች የእርዳታ ፕሮግራም በበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ እዚህ ላይ here ይጫኑ።

***

ጉዳዮን በተመለከተ ህጋዊ ምክር ቢያስፈልጎ ሊጋል ኤድ (Legal Aid) ጋር ተገናኙ። በ ኖርትዌስትና ሳውዚኢስት (Northwest እና Southeast) ያሉት መስርያ ቤቶቻችን ለህዝብ የተዘጉ ቢሆኑም፤ በስልክና በኦንላይን ክፍት ነን። አገልግሎታችንን ለማግኘት በስልክ ቁጥር 202) 628-1161 በመደወል ወይም በኦንላይን online በመግባት ያመልከቱ።